# ግንቦት 97 ሁለት ዓመት ሆነው

## የሕዝብ ድምጽ ይከበር!!! የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ የትግል ታሪክ ነው ቢባል ስህተት አይደለም። በተለይ ላለፉት 50 ዓመታት በዓጼው፤ በደርግና በወያኔ የግፍ አገዛዝ ላይ ለመብቱ፤ ለነፃነቱና ለሀገሩ ክብር ታግሏል። ዛሬም እየታገለና መስዋዕትነት እየከፈለ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ረሃብ፤ በሽታ፤ ድንቁርናና ድህነት የዘር ግንዱ ይመስል አብረውት ከኖሩ ዘመናት ተቆጥረዋል። እውን የሰማዩ ገሃነም ኑሮ ከሀገራችን የሥቃይ ኑሮ ይበልጣልን? ሃገሪቱ የሰው ልጅ ላጠፋው ጥፋት ሁሉ ቅጣቱን እንድትቀበልባት የተመረጠች ምድር ስትመስልና ሰቆቃውና መከራ በየጊዜው ሲፈራረቁ አምባገነን መንግሥታት ግን ይበልጥ እንክብካቤ እያገኙ ለመሄዳቸው የገፈቱ ቀማሽ ለሆነው ሕዝብ ነጋሪና መስካሪ አያሻውም። የሕዝብን የዓመታት ትግል በመመርኮዝ ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጡ በኋላ ያሳለፉትን መከራና ችግር የብቻቸው አድርገው እነሱ ካማረባቸው ሕዝብ ያማረበት፤ እነሱ ከጠገቡ ሕዝብ የጠገበ፤ እነሱ ከደላቸው ሕዝብ የደላው የሚመስላቸው መሪዎች፤ የሀገሪቱ ዕድገት ዓመታዊ ገቢ ወደ እነሱ ኮሮጆ በገባው ልክ ተሰልቶ የሚነገርበትን ዓይን ያወጣ አገዛዝ በደርግም አይተናል። በወያኔም ተደግሟል። ደርግ በዓፄው አገዛዝ ላይ ዳር እስከ ዳር ያመፀውን ሕዝብ ምርኩዝ በማድረግ ሥልጣን ጨብጦ «ከቆራጡ መሪ ጋር ወደፊት»ን ዘመረብን። ወያኔ በፋሽስታዊው አገዛዝ ላይ ያመፀውን ሕዝብ ምርኩዝ በማድረግ ሥልጣን ጨብጦ «ሁሉንም ነገር በሕገ መንግሥቱ ጥላ ሥር» እያለ እያፌዘብን ይገኛል። ዛሬ ደግሞ በወያኔ አገዛዝ ላይ ያመፀውን ሕዝብ ምርኩዝ በማድረግ ገና ለሥልጣን ሳይታደሉ ዕቅዳችንና ሂደታችን የወያኔን ሕገ መንግሥት መሠረት ያደረገ ነው እየተባልን ነው።

ግንቦት 97 በኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግል ታሪክ ውስጥ ከየካቲቱ 66 ቀጥሎ የተከሰተ ከፍተኛው የለውጥ ምዕራፍ ነበር። የየካቲቱ አብዮት የፊውዳሉን ሥርዓት ገርስሶ ፋሺዝምን ሊያነግስ የግንቦት 97 ማዕበል ግን ወያኔን እንደያዘ ሁለት ዓመት አስቆጥሯል።

በወያኔ የገጠር መሠረተ ልማት ፕሮግራም አበሳውን ያየውና እያየ ያለው አርሶ አደር፤ በማዳበሪያ ሰበብ፣ በቅይረ ብሄራይ ህይወታት ፕሮግራም ተፈጥሮዓዊ ሰብሉን እያጣ ከጊዜ ወደ ጊዜ አፈሩ ፀጋውን እየነሳው አዝመራው ፍሬ አልባ እየሆነበት በስሙ ብቻ ስለ ዕድገትና ብልጽግና መደስኩሩ ያንገበገበው አርሶ አደር፤ አገዛዙ ለአለፉት 14 ዓመታት በፈጠራቸው ውስብስብ የአስተዳደርና የግፍ አገዛዝ በተጨማሪ እየቀረበለት ያለው ገፀ - በረከት ረሃብ፣ በሽታና ስቃይ ያንገፈገፈው አርሶ አደር ለወያኔ አልገዛም ያለበትና ማንነቱን ያስመሰከረበት ወቅት ግንቦት 97 ነው።

ቅድመ ዝግጅትና ተገቢ ጥናት ሳይደረግበት ተግባራዊነቱ ትውልድን ለማቀጨጭ ተወጥኖ የተዘጋጀው የወያኔ አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ሕፃናት ያለ ዕድሜያቸው የሀገር ሸክም፣ የቤተሰብ ተጧሪ እንዲሆኑና በጨቅላ አዕምሮአቸው የወደፊት ብሩህ ተስፋ እንዳይኖራቸው፣ ተስፋ ቆርጠው ስለ ሀገራቸውና ሕዝባቸው ከማሰብ ይልቅ "የተሳካለት" ስለ ስደት ፣ ያልሆነለትም ስለ ሌብነትና ዘረፋ እንዲያስብ የተዘጋጀለት ወጥመድ በተጨማሪ ወደፊትም ለሀገሪቱ በማንኛውም መስክ ብቁ ዜጋ ሀገር ተረካቢ ትውልድ እንዳይኖር የተሸረበው የወያኔ ሤራ በሕብረተሰቡና በተተኪው ትውልድ ውስጥ ያስከተለው ተቃውሞ እያደር ተወጥሮ የነበረው የቁጭት ስሜት የፈነዳበት ወቅት ግንቦት 97 ነው።

ለወያኔ አንዱን ዘር በሌላው፡ አንዱን ጐሳ ከሌላው፡ አንዱን ሃይማኖት ከሌላው ለማጋጨት፤ ለማተራመስ፤ ለማናከስ በተለያየ ጊዜ ለተወጠነው የወያኔ ከፋፋይ ፖሊሲ ሳለመንበርከክና መሳሪያ ላለመሆን እርስ በርሱ እየተከባበረ ከዚህ መርዘኛ የወያኔ ከፋፋይ አዙሪት ሳይሰነቀር አንድ ሕዝብ፡ አንድ ዜጋ፡ አንድ ኢትዮጵያዊ መሆኑን መላው ሕዝብ ያሳየበት ጊዜ ቢኖር ግንቦት 97 ነው።

ለአለፉት 14 ዓመታት በግፍ፡ በስቃይ፡ በበሽታ፡ በረሃብ ፍዳውን እያየ ጉዞህ እኛ በምንልህ መስመር ብቻ እንዲጓዝ ፤ ዓይንህ እኛ የምናሳይህን ብቻ እንዲያይ፤ ጆሮህ እኛ የምንልህን ብቻ እንዲሰማ፤ አፍህ ተግባሩ እኛን ማሞገስ ብቻ ተብሎ ህዋሳቱ ተለጉመው ፡ ፍትህና ነፃነቱን የተቀማው ሕዝብ እምቢኝ ብሎ የበላይነቱን ያሳየበት ወቅት ቢኖር ግንቦት 97 ነው።

«ይታያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ»፤ «ሃያ ሆ...ሆ ዛሬ ነው ድሌ»፤ «ዋይ ዋይ ወያኔ»፤ «ሞት ለወያኔ» የተዘመረበት፡ የተፈከረበት፡ የተገጠመበት በአንፃሩ «ኢትዮጵያ ሀገሬ የተዜመበት»፤ «ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም» የተስተጋባበት፤ ሰንደቅ ዓላማችን ክብሩን ያገኘበት ወቅት ቢኖር ግንቦት 97 ነው።

የ14 ዓመታት የግፍ አገዛዝ፤ እስራት፤ ግርፋት፤ ግድያ ለአንዴም ለሁሌም ማብቃት አለበት፤ መብቴን፤ ነፃነቴን፤ ሀገሬን ክብሬን ብሎ ዳግም የካቲትን ሕዝባችን የወለደበት ጊዜ ቢኖር ግንቦት 97 ነው።

ግንቦት 97 ሲባል የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩ፤ ለዳር ድንበሩ፤ ለነፃነቱ ከፍተኛውን ተጋድሎ ያደረገበትና መስዋትነት የከፈለበት በመሆኑ ነው የሚታወሰው። የሕዝብ የ14 ዓመት የነጻነትና የመብት ተጋድሎ ውጤት የፈጠረውን የግንቦት 97 እንቅስቃሴ ስናስታውስ በፍልሚያው ሜዳ የተሰዉትን እየዘከርንና ለፈሰሰውም ደም ወያኔን ተጠያቂ እያደረግን፤ ወያኔ በአገዛዝ ዘመኑ ደብዛቸውን ያጠፋቸውን ሁሉ የት እንደደረሱ እየጠየቅን፤ አካለ ስንኩል ያደረጋቸውን እያበረታታን፤ የስደት ኑሮ ቀማሽ ያደረጋቸውን አንድነታችን ይጠንክር እያልን ፤ በየማጎሪያው የሚያሰቃያቸውን የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ መፈታት እየታገልን በአጠቃላይም ለሀገራችንና ለሕዝባችን ዘለቄታዊ ሰላምና አንድነት የትግል አርማችንን እያደስን መሆን ይኖርበታል።

በግንቦት 97 የምርጫ ትርዒት የረዥምም የአጭርም ጊዜ የፖለቲካ ተመክሮ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ውሳኔያቸውና አካሄዳቸው ሕዝቡን እየተከተሉ ነበር። ሕዝቡ በንቃቱና በፀረ-ወያኔ አቋሙና ጽናቱ ከሁሉም በልጠና ልቆ በይፋ የታየበት ወቅት ቢኖር ግንቦት 97 ነው። ይህ ጽናትና ንቃት ዛሬም ከሕዝብ ጋር አለ። የጐደለው ቢኖር የጠንካራ መሪ ድርጅት እጦት ነው።  የ97ቱ የግንቦት ወር በፖለቲካ ሂደቱ የተሳተፉ የፖለቲካ ድርጅቶች (በተለይ ቅንጅትና ኅብረቱ) ምን እንደሚያደርጉ ግራ የገባቸው መሆኑ በግልጽ የታየበት፤ በአፋጣኝ የወቅቱን የትግል አቅጣጫ መስመር በማስያዝ ሕዝቡ በድምጹ ያገኘውን የበላይነት ለድል ማብቃት ሲጠበቅባቸውና የሕዝቡን ኮቴ እየተከተሉ እንኳ ትግሉን ይበልጥ ማቀጣጣል  ሲገባቸው ዳር ሆነው መመልከትን ያጐሉበት ወቅት ነው። እንደመረጥከን አለን ብለው አፋጣኝ መልስ ሊሰጡና ትግሉን በበላይነት ሊወጡም አልተዘጋጁም ነበር። እንደውም ሕዝቡ ለመጨረሻው ፀረ-ወያኔ ፍልሚያ የተዘጋጀበትንና በጉጉት እየተጠባበቀው የነበረውን «የሙት ቀን አድማ» በማኮላሸት ዋናውን ሚና የተጫወቱት ሕዝብ ድምጹን የሰጣቸው መሪዎች መሆናቸው ግንቦት 97ን በልዩ ስሜት እንድናስታውሰው ያደርገናል።

በአጠቃላይ የ30 ዓመት ስቃይ፡ በዘመነ ወያኔ ደግሞ የ14 ዓመት የሕዝብ ትግል የወለደው ግንቦት 97 ምርጫ «ነፃነት ወይስ ባርነት» እንደተባለው አንድምታው «ወያኔ ወይስ ሌላ» ተብሎ ነበር የቀረበው። በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያኔም ይሁን አሁን ይህንን በሀገርና በሕዝብ የመጣ

አሸባሪ፡ ወራሪ አገዛዝ ገፍትሮ መጣል ነውና ትግሉ ከቀረበለት የወያኔ ኮሮጆ ይልቅ እራሱ ውስጥ አጭቆ ነው ቅንጅትና ኅብረትን የመረጠው። “የፖለቲካ ሥልጣን ሕዝብ ለመረጠው ክፍል ይተላለፍ” እና “የሕዝብ ድምጽ ይከበር”ም ቀጣዩ መፈክር ሆነ። ዛሬም የሕዝቡ መፈክር ነው። መስዋዕትነትና ደም የተከፈለበት መፈክር። እስር፡ ጭፍጨፋ ፡ መከራ፡ ግድያ እየተከፈለበት ያለ መፈክር።

ወያኔ በግንቦት 97 ምርጫ በውኑም በህልሙም ይፈጠራል ብሎ ያልገመተው ሽንፈት ስለገጠመው እንደዚያ ቀን ዲሞክራሲንና ምርጫን የሚረግምበት ቀን እንደማይኖር ግልጽ ነበር። ቅንጅት አብላጫውን ኅብረት ከፊሉን በአጠቃላይ ተቃዋሚ ኃይሎች አብላጫውን የሕዝብ ድምጽ በማግኘታቸው ወያኔ ሙሉ በሙሉ በመሸነፉ ሁሉም ተደሰተ። «ድሌ ዛሬ ነው ድሌ» ተዘመረ። እንዴት ተደርጐ ሥልጣን ከወያኔ ወደሕዝብ፤ እንዴት ተደርጐ ሀገር ከወያኔ ወደሕዝብ፤ እንዴት ተደርጐ ፍቅር ከወያኔ  ወደሕዝብ። “ሽንኩርት የባህሪውን ይሸታል” እንዲሉ ወያኔ ባህሪው ተገለጠ። የዲሞክራሲ ጭምብሉ ወለቀ። አደባባይ ወጣ። የቀበሮ ባህታዊነቱን ራሱ ተናገረ። ራሱ በራሱ መሰከረ። የምርጫውን ኮሮጆ በጥይት በጣጠሰው። ደም ጠጣ። “እኔ ልዝፈን እናንተ አጨብጭቡ፤ እኔ ልዝፈን እናንተ እስክስታ ውረዱ፤ እኔ እንጂ እናንተን ማን ሠርገኛ አደረጋችሁ” አለ። የግንቦት 97ን የሕዝብ ድል በደም ቀባው። በሕዝብ ደም ምርጫ 97ን አሸንፌሃለሁ ብሎ ፃፈ። በሕዝብ ደም አገዛዜን የሙጥኝ አለ።

የቅንጅት መሪዎች ለእስር ከተዳረጉ በሁዋላና በተለይም በወያኔ አረመኔአዊ ድርጊት የተደናገጡ ትግሉ ወዴት? ምን መደረግ አለበት? ብሎና መክሮ የትግል አቅጣጫን በመቀየር በገደል አፋፍ ላይ ቆሞ የነበረውን ወያኔ ገፍትሮ ወደ ጉድጓዱ ለመክተት በጋራ ከመተባበር ይልቅ ከቆመበት የገደል አፋፍ ተሰቦ እንዲወጣ ገመድ ያቀበሉ ብቅ ያሉበት ወቅት እንደነበር በይፋ ተስተውሏል።

ዛሬ የግንቦት 97 ሁለተኛ ዓመትን ስናስታውስ መሪ መፈክራችን “የሕዝብ ድምጽ ይከበር” ፡ “የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ” መሆኑን ከፍ በማድረግ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያና መላው ሕዝባችን ላይ በወያኔና አጫፋሪውቹ የተደቀነውን አስከፊ አደጋ እንዴት እንከላከለው? ልዩነታችንን አቻችለን፡ የጋራ ትግላችንን በጋራ አንድ ሆነን ተሰባስበንና አብረን ለመነሳት ምን ማድረግ አለብን? ይህ በቋፍ ያለ አገዛዝ ሳይሞቀው እንደቀዘቀዘው እናኮማትረው፡ ለዚህም ኃይልና አለኝታችን ሕዝባችን ነውና ከሕዝብ ጋር ሆነን፡ ብሶቱ ብሶታችን ሁኖ፡ ስቃዩ ስቃያችን ሁኖ እየተካሄደ ያለውን ፀረ-ወያኔ ትግል በበላይነት ለመምራት ወያኔን መለመን ሳይሆን ለምኖን እንዲንበረከክ ያለንበትን ጉዞና አቅጣጫ ቆም ብሎ መመርመር ከሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፡ የብዙሃን ድርጅቶች፡ የሃይማኖት ተቋሞች፡ ታዋቂ ግለሰቦች፡ ምሁራን፡ በውጭው ዓለም ተበትኖ ካለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ብዙ ይጠበቃልና ቀና ብለን ሀገራችንንና ሕዝባችንን እንመልከት።

**የሕዝብ ድምጽ ይከበር!!!**

**የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

**ከአቶ ተማቹ** **ግንቦት 02፣ 1999 ዓ.ም.**